# Saints on the Go
# ቅዱሳን በጉዞ ላይ

## ደቀ መዝሙር ቁጥር አንድ - ማስተማሪያ

የክርስትና መሰረታዊ ትምህርቶችን ማስተማሪያ መመሪያ

## ማውጫ


መግቢያ ........ 2

*ትምህርት አንድ* ........ 3

የእግዚአብሔር ቃል - መጽሐፍ ቅዱስ ........ 3

*ትምህርት ሁለት* ........ 6

ሰው ከውድቀት በፊት ........ 6

*ትምህርት ሦስት* ........ 9

ሰው ከውድቀት በኋላ ........ 9

*ትምህርት አራት* ........ 11

ድነት ወይንም መዳን ........ 11

*ትምህርት አምስት* ........ 14

የሰው ማንነት በክርስቶስ ........ 14

*ትምህርት ስድስት* ........ 16

እምነት ........ 16

*ትምህርት ሰባት* ........ 18

መጽደቅ ........ 18

*ትምህርት ስምንት* ........ 20

ቅድስና ........ 20

*ትምህርት ዘጠኝ* ........ 23

ጸሎት ........ 23

*ትምህርት አሰር* ........ 26

መከራ ........ 26

*ዋቢ መጻሕፍት* ........ 29

## መግቢያ

*መጽሐፉ ለመምህሩ ማስተማሪያ እና ለተማሪው መከታተያ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ስለ ሆነ፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህሩም ሆነ ተማሪው መጽሐፉን መያዝ ይኖርባቸዋል።*

*ይህ መጽሐፍ አስር የክርስትና መሠረታዊ አስተምህሮዎችን በአርዕስትነት የያዘ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ትምህርት ደግሞ የሚከተሉትን ነጥቦች አካትቶአል፥*

1. ***የትምህርት ርዕስ፡-*** *ይህ የትምህርቱ ርዕስ ነው።*
2. ***የንባብ ክፍል፡-*** *ይህ የትምህርቱን ዋና አሳብ የያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ የተገለጸበት ነው። መምህሩ በትምህርቱ ወቅት በመጀመሪያ ለተማሪዎቹ ማንበብ ወይንም እንዲነበብ ማድረግ ይገባዋል፤ እንደ አስፈላጊነቱም በትምህርቱ መካከልና መጨረሻ ላይ ተደጋግሞ ቢነበብ መልካም ነው።*
3. ***ረዳት ጥቅሶች፡-*** *ይህ የትምህርቱን ዋና አሳብ የያዘው የመጽሐፍ ቅዱስ ረዳት ጥቅስ የተገለጸበት ነው።*
4. ***መግቢያ፡-*** *ዓላማው እያንዳንዱን ትምህርት ማስተዋወቅ ወይንም የመግቢያ አሳብ መስጠት ነው።*
5. ***የቃሉ ትርጉም፡-*** *ይህ ክፍል በርዕስ ጉዳይነት ለቀረበው አሳብ (ቃል) ፍቺ የሚሰጥ ነው። ፍቺው ቃሉ በትምህርቱ ዐውድ ውስጥ ያለውን ትርጉም የሚያመለክት ነው።*
6. ***የትምህርቱ ዋና አላማ፡-*** *ይህ ክፍል የእያንዳንዱን ትምህርት ዓላማዎች የሚያመለክት ነው። የትምህርቱን ጭብጥ ስለሚያስረዳ፣ መምህሩ ለእያንዳንዱ ትምህርት ሲዘጋጅ ይመራዋል፣ በሚያስተምርበትም ወቅትም ሆነ በመጨረሻ ለተማሪዎቹ ያስጨበጠውን ለመገምገም የረዳዋል። ተማሪዎቹም ያገኙትን ግንዛቤ ይመዝኑበታል።*
7. ***ትምህርቱ፡-*** *ይህ የትምህርቱ ዋና ክፍል ነው። የትምህርቱ ዋና ነጥቦች በጥያቄና መልስ መልክ ተዘርዝረው ቀርበውበታል። በዚህ መልክ የቀረበው መምህሩ ለማስተማር እንዲቀለው እና ተማሪዎቹም የተማሩትን ለማስታወስ እንዲረዳቸው ነው። በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት ነጥቦች በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተሰጥቶባቸዋል።*
8. ***ማጠቃለያ፡-*** *በመግቢያ፣ በትርጉም፣ በዋናው ትምህርት ውስጥ የተነሡትን አሳቦች ሁሉ ጠቅለል ባለ መልኩ ያቀርባል ወይንም ማጠቃለያ ይሰጣል።*
9. ***ጥያቄዎች፡-*** *የጥያቄዎች ትኩረት በክፍሉ የተካተቱትን ዋና ዋና አሳቦች እና ትምህርቱ ከሕይወት ጋር ባለው ተዛምዶ ላይ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች መምህሩ የተማሪዎቹን ግንዛቤ ለመገምገም ይረዳዋል።*
10. ***የሚጠና ጥቅስ፡-*** *ይህ ክፍል የትምህርቱ ዋና አሳብ የተገለጸበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የያዘ ሲሆን፣ ጥቅሶቹን ተማሪዎቹ በቃላቸው ሊያስታውሷቸው ይገባል። አንድ ትምህርት አልቆ ሌላው ሲጀመር መምህሩ ተማሪዎቹ ጥቅሱን ማስታወሳቸውን ማረጋገጥና እርሱም ደግሞ በቃሉ ባመናገር አርዓያ መሆን ይኖርበታል።*

*ከዚህ በተጨማሪ ትምህርቱን ለማዘጋጀት የተጠቀምንባቸውን የተዘረዘሩትን ዋቤ መጻሕፍትን በጥልቀት በማየት፤ መምህሩም ሆነ ተማሪዎቹ ለተጨማሪ ንባብ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።*

*እንግዲህ የቃሉ ባለቤት መንፈስ ቅዱስ መምህራንንና ተማሪዎችን እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት ይባርክ ዘንድ ጸሎታችን ነው።*

# ትምህርት አንድ

## የእግዚአብሔር ቃል - መጽሐፍ ቅዱስ

### የንባብ ክፍል

*መዝሙረ ዳዊት 119:10*

**"በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ፥ ከትእዛዝህ አታርቀኝ።"**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

መዝሙረ ዳዊት 19:7-11፣ 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:16-17

### መግቢያ

የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሰጣቸው ታላላቅ ስጦታዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ራሱን ገልጿል። በተጨማሪም፣ ለሰው ልጆችና በአጠቃላይ ለዓለም ያለውን አሳብና ዕቅድ አሳውቋል። በዚህ ክፍል የእግዚአብሔርን ቃል ማን እንደጻፈው፣ እንዴት እንደተጻፈ፣ ለምን እንደተጻፈ፣ ባሕርያቱን፣ የተመሰለባቸውን ነገሮችና ቃሉን ማንበቡ ለምን እንደሚጠቅም በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን።

### የቃሉ ትርጉም

የእግዚአብሔር ቃል፥ የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን 66 መጻሕፍትን አጠቃልሎ የያዘውን መጽሐፍ ቅዱስን ያመለክታል።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የእግዚአብሔርን ቃል ምንነት ማሳወቅ፣
2. የእግዚአብሔር ቃል ያለውን ሥልጣንና ተአማኒነት ማሳየት፣
3. እያንዳንዱ አማኝ ለቃሉ የሚገባውን አክብሮት እንዲሰጥ፣ እንዲያነቡትና ለዕለት ተዕለት ኑሮአቸው መመሪያ እንዲያደርጉት ማበረታታት ነው።

### ትምህርቱ

1. የእግዚአብሔር ቃል፥
    i. የተጻፈው የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ነው፣
       2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:21፤ 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:16-17
    ii. ለሰዎች የተሰጠ ነው፣
       ኦሪት ዘዳግም 29:29፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 23:2
    iii. እግዚአብሔር እራሱን ለሰዎች የገለጠበት መንገድ ነው፣
       ወደ ሮሜ ሰዎች 16:25-26
    iv. በሰው ህይወት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ነው፣
       2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:16፣ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:23
    v. ምንም ስህተት የሌለበት ፍጹም መጽሐፍ ነው፣
       1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:3

2. የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው፥
    i. እግዚአብሔር እውነቶችን በተለያየ መንገድ ገልጦ፣
       ወደ ዕብራውያን 1:1-3
    ii. የእግዚአብሔር ሰዎች እውነቱን ተቀብለው፣
       የዮሐንስ ራእይ 1:19
    iii. በጽሑፍ አስፍረው አስተላለፉት፣
       2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:21
3. የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው፥
    i. 1,500 ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተጻፈ ሲሆን፣ 66ቱም መጽሐፍት በአንድ ጊዜ የተጻፉ አይደሉም፣
    ii. በተላያየ ጊዜያት የተጻፈ መጽሐፍት ቢሆንም፣ መልእክቱ ወጥነት እና እንድነት ያለው መጽሐፍ ነው፣
    iii. ከአርባ ባላነሱ ሰዎች፣ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተጻፈ፣
4. የእግዚአብሔር ቃል ለተለያዩ ነገሮች ይጠቅማል፥
    i. አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ወይንም ዳግም ልደት ያስገኛል፣
       ወደ ሮሜ ሰዎች 10:17፣ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:23
    ii. ለመንፈሳዊ ሕይወት ምግብ ይሆናል፣
       1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:3
    iii. ለሕይወት መመሪያ ይሆናል፣
       መዝሙረ ዳዊት 119:105
    iv. ይቀድሳል፣
       የዮሐንስ ወንጌል 17:17
    v. ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናትና በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማል፣
       2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:16-17
    vi. አስተዋይ ያደርጋል፣
       መዝሙረ ዳዊት 119:97-104
    vii. ለስኬት ይጠቅማል፣
       መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 1:7
5. የእግዚአብሔር ቃል የተለያዩ ባሕርያት አሉት፥
    i. ሕያው ወይንም ዘላለማዊ ነው፣
       1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:23
    ii. ኃይል አለው፣
       ትንቢተ ኤርምያስ 23:29
    iii. የሚሠራ ነው፣
       ወደ ዕብራውያን 4:12
    iv. ውስጥን የሚመረምር ነው፣
       ወደ ዕብራውያን 4:12
6. የእግዚአብሔር ቃል በተለያዩ ነገሮች ተመስሏል፥
    i. በወተት፣
       1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:3
    ii. በሰይፍ፣
       ወደ ዕብራውያን 4:12
    iii. በመስተዋት፣
       የያዕቆብ መልእክት 1:22-24
    iv. በእሳት፣
       ትንቢተ ኤርምያስ 23:29
    v. በመዶሻ፣

ትንቢተ ኤርምያስ 23:29

vi. በመብራት፣

መዝሙረ ዳዊት 119:105

vii. በዘር፣

1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:23

7. የእግዚአብሔር ቃል - መጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል፥
   i. የብሉይ ኪዳን፥
      i. 5 - የሕግ መጽሐፍት፣
      ii. 12 - የታሪክ መጽሐፍት፣
      iii. 5 - የቅኔ መጽሐፍት፣
      iv. 17 - የትንቢት መጽሐፍት፣
         1. 5 - የታላላቅ ነብያት መጽሐፍት፣
         2. 12 - የታናናሽ ነብያት መጽሐፍት፣
   ii. የአዲስ ኪዳን፥
      i. 4 - የወንጌል መጽሐፍት፣
      ii. 1 - የተሪክ መጽሐፍ፣
      iii. 21 - የመልክቶች መጽሐፍት፣
      iv. 1 - የትንቢት መጽሐፍ፣
8. የእግዚአብሔር ቃል በዚህ መንገድ ቢነበብ ጥሩ ነው፥
   i. ምቹ ጊዜን በመምረጥ፣
   ii. በየዕለቱ ያለማቋረጥ፣
   iii. በጽሞና እያሰላሰሉ፣
   iv. ማስታወሻን በመጻፍ፣
   v. በተገነዘብነው እውነት ለመኖር እግዚአብሔር እንዲረዳን እየጸለይን፣

## ማጠቃለያ

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስህተት አልባ እና የራሱ የእግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ ያለበት መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ብቸኛው የህይወታችን መመሪያ እና መልህቅ ስለሆነ፤ ልናነበው፣ እለት እለት ልናሰላስለው፣ በእለት ተእለት ኑሮአችን ልንመራበት ይገባል።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ቃል ምንድን ነው?
2. የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጣቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
3. የእግዚአብሔር ቃል በምን ተመስሏል?

## የጥናት ጥቅስ

**"ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።"** *የያዕቆብ መልእክት 1:22*

# ትምህርት ሁለት

## ሰው ከውድቀት በፊት

### የንባብ ክፍል

*ኦሪት ዘፍጥረት 1:26-27*

**"እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።"**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ኦሪት ዘፍጥረት 9:6፤ ወደ ሮሜ ሰዎች 8:29፤ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 15:42-57፤ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:15-16

### መግቢያ

የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው። ከፈጠራቸው ፍጥረት መካከል አንዱ ሰው ነው።የሰው አፈጣጠር ግን ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የተለየ ነው። የመለየቱ ምክንያት በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው፤ ያበጀውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ከሌሎች ፍጡራን የተለየ መብትንና ክብርን አግኝቶአል። ይህ የተለየ መብቱ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትና ግንኙነት ማድረግ መቻሉ ነው።

### የቃሉ ትርጉም

**"ሰው ከውድቀት በፊት"** - የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋራ የነበረውን ህብረት ከማጣቱ በፊት የነበረበት ሁኔታ።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. ስለ ሰው አፈጣጠር ማወቅ፣
2. ሰው ከፍጥረት በፊት የነበረበትን ሁኔታ መረዳት፣
3. ሰው የተፈጠረበትን ዓላማ ማጥናት፣

### ትምህርቱ

1. የሰው ማንነት፥
   - i. ሰው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠረ ነው። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማድረግ ይችላል። (ኦሪት ዘፍጥረት 1:26)
   - ii. ሰው ሥጋው ከአፈር የተሠራ ነው። (ኦሪት ዘፍጥረት 2:7)
   - iii. ሰው የሕይወትን እስትንፋስ ያገኘው ከእግዚአብሔር ነው። በመሆኑም ነፍሱና መንፈሱ ዘላለማዊነትን አገኙ። (ኦሪት ዘፍጥረት 2:7)
   - iv. ሰው ወንድና ሴት ተደርጎ ተፈጥሯል። በመሆኑም በምድር ላይ ሊበዛ ችሎአል።

(ኦሪት ዘፍጥረት 1:27)

v. ሰው ከእግዚአብሔር ከፈጣሪው ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የነበረው ኃጢአትን የማያውቅ ፍጡር ነበር። (ኦሪት ዘፍጥረት 2:19-20)

2. ሰው የተፈጠረበት ዓላማ፥
   i. እግዚአብሔር ለክብሩ ፈጥሮትል፤
   ii. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ለማድረግ፤
   iii. የእግዚአብሔር ማንነት በሰው ውስጥ እንዲታይ፤
   iv. እግዚአንሔር ሰውን ምድርን እንዲያበጅ እና እንዲገዛ ፈጠረው፤
   v. እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለው ዓላማ ይፈጸምበት ዘንድ፤
   (ትንቢተ ኢሳይያስ 43:6-7፤ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:11-12፤ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:31)

3. የሰው አኗኗር ከውድቀት በፊት፥
   i. ነጻ ፈቃድና ምርጫ ነበረው
   (ኦሪት ዘፍጥረት 2:26፣ 3:1-6)
   ii. በተመቸ ስፍራ በዔድን ገነት ይኖር ነበር
   (ኦሪት ዘፍጥረት 2:8)
   iii. በፍጥረት ሁሉ ላይ ገዢ ነበር
   (ኦሪት ዘፍጥረት 1:27-28)
   iv. የዔድን ገነት ጠባቂና ተንከባካቢ ነበር
   (ኦሪት ዘፍጥረት 2:15)
   v. ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበረው
   (ኦሪት ዘፍጥረት 2)
4. የሰው አፈጣጠር ይዘት፥
   i. ሰው እውቀት፣ ስሜት፣ ፈቃድ አለው። ማሰብ የሚችል የራሱ የምርጫ ነፃነት ያለው ፍጡር ነው።
   (ኦሪት ዘፍጥረት 2:16-17)
   ii. ሰው ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ አሉት።
   (1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:23)

## ማጠቃለያ

ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ ህያው፣ ክቡርና ልዩ ፍጡር ነው። በእግዚአብሔርም እጅግ የተወደደ ፍጡር ነው። እግዚአብሔርም በመልኩና በአምሳሉ የፈጠረው፤ ስጋ፤ ነፍስና መንፈስ ያለው ፍጡር ነው። ሰው የራሱ የሆነ እውቀት፣ ስሜትና ፈቃድ አለው። ሰው ከውድቀት በፊት ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር መልካምና ህያው የሆነ ግንኙነት እና ህብረት የነበረው ፍጡር ነው።

## ጥያቄዎች

1. የሰው አፈጣጠር እንዴት ነው?
2. ሰው ለምን ዓላማ ተፈጠረ?
3. ሰው ከውድቀት በፊት አኗኗሩ እንዴት ነበር?
4. የሰው አፈጣጠር ይዘት እንዴት ነው?

## የጥናት ጥቅስ

**“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።”** *ኦሪት ዘፍጥረት 1:27*

**“እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።”** *ኦሪት ዘፍጥረት 2:7*

# ትምህርት ሦስት

## ሰው ከውድቀት በኋላ

### የንባብ ክፍል

*ኦሪት ዘፍጥረት 3:9-11*

**"እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፦ በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ፥ ተሸሸግሁም። እግዚአብሔርም አለው፦ ዕራቁትህን እንደ ሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝሁህ ዛፍ በውኑ በላህን?"**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ወደ ሮሜ ሰዎች 2:1-11፤ ወደ ሮሜ ሰዎች 3:10-26፤ ወደ ሮሜ ሰዎች 5:12-19፤ የያዕቆብ መልእክት 1:12-15፤ 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 1:8-10

### መግቢያ

የመጀመሪያው ሰው አዳም ኃጢአትን በመሥራቱ ምክንያት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ፤ መልካም የነበረው ፍጥረት ሁሉ ተበላሸ። በዚህ ጥናት፥ ሰው ከውድቀት በኋላ፤ ውድቀት ስላመጣበት ኃጢአትና፣ ኃጢአቱ ስላስከተለው ውድቀት እናጠናለን።

### የቃሉ ትርጉም

**"ሰው ከውድቀት በኋላ"** - የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ከተለየ በኋላ፤ ስለተከተለው የመውድቁ ውጤት እና የኑሮው ሁኔታ። ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሀሳብና መለኮታዊ ፈቃድ፤ እንዲሁም ከተፈጠረበት ዓላማ ውጭ ማሳት ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የኃጢአትን አመጣጥና ምንነት ማስረዳት፣
2. በውድቀት ምክንያት የሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት መቋረጡን ማየት፣
3. ከውድቀት በኋላ ኃጢያትና ያስከተለውን ውጤት ማጥናት፣

### ትምህርቱ

1. የኃጢአት ምንነት፥
   i. ኃጢአት ከእግዚአብሔር ክብር መጉደል ነው፤
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23)
   ii. ኃጢአት እግዚአብሔር የደነገጋቸውን ሕግጋት መተላለፍ ነው፤
   (የያዕቆብ መልእክት 2:10)
   iii. ኃጢአት መልካም አለማድረግ ነው፥ ማለትም ማድረግ የሚገባን መልካም ነገር በቸልተኝነት ሳያደርጉ መቅረት፤
   (የያዕቆብ መልእክት 4:17)

iv. ኃጢአት ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ወይንም በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ነው፤ (1ኛ የዮሐንስ መልእክት 3:4)

2. የኃጢአት ጅማሬ፥
   i. ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ለመተካከል አስቦ ባመፀ ጊዜ፤ (ትንቢተ ኢሳይያስ 14:12-14)
   ii. የመጀመሪያዎቹ ሰዎች፣ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ አትብሉ የተባሉትን የዛፍ ፍሬ በበሉ ጊዜ፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 3:6-7)
3. የኃጢአት ዓይነቶች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም፥
   i. የውርስ፥ ሰው የአዳም ልጅ በመሆኑ ምክንያት በውርስ የተላለፈበት ኃጢአት፤ (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:12)
   ii. የድርጊት፥ ሰው በባሕሪው ኃጢአተኛ በመሆኑ ምክንያት የሚፈጽመው ኃጢአት፤
4. የኃጢአት ውጤቶች፥
   i. የስጋ ሞት፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 2:17)
   ii. መንፈሳዊ ሞት፥ ማለትም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ የግንኙነት መበላሸት፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 3:19፣ ወደ ዕብራውያን 9:27፣ የማቴዎስ ወንጌል 10:28፣ የሉቃስ ወንጌል 12:4-5)
   iii. ዘላለማዊ ሞት፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 3:24፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-2)
   iv. በሰዎች መካከል ያለ የግንኙነት መበላሸት፤ (ኦሪት ዘፍጥረት 3)
   v. ርግማን (ኦሪት ዘፍጥረት 3:14-21)

## ማጠቃለያ

ሰው ከውድቀት በኋላ ከእግዚአብሔር ተለየ። የሰው ልጅ በሙሉ በኃጢአት ወደቀ፣ የእግዚአብሔር ክብር ጎደለው። በዚህም ምክንያት፥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ፣ መልካም ሆኖ የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ተበላሸ።

## ጥያቄዎች

1. ለሰው ልጅ መውደቅ ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
2. ኃጢአት ምንድን ነው?
3. ኃጢአት መቼ ተጀመረ?
4. የኃጢአት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
5. የኃጢአት ውጤቶች ምንድን ናቸው?

## የጥናት ጥቅስ

**"ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።"** *ኦሪት ዘፍጥረት 2:17*

**"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤"** *ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23*

# ትምህርት አራት

## ድነት ወይንም መዳን

### የንባብ ክፍል

*የሐዋርያት ሥራ 4:12*

**“መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።”**

*የዮሐንስ ወንጌል 3:16*

**“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ትንቢተ ሕዝቅኤል 36:26-27፣ ትንቢተ ሶፎንያስ 1፣ የዮሐንስ ወንጌል 3:16-17፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 1:16-17፣ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:26-31፣ 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1:6-10

### መግቢያ

በዚህ ጥናት ኢየሱስ ለኃጢአት መድኃኒት ይሆን ዘንድ የከፈለውን ታላቅ መሥዋዕትነት እንዲሁም ከዚህ የተነሳ የሰው ልጅ ያገኛቸውን ጥቅሞች እንመለከታለን።

### የቃሉ ትርጉም

ድነት፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ የዘላለም ሕይወት ነው፤ ከኃጢአትና ከእግዚአብሔር ቁጣ መዳን ነው፤ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት እንዲስተካከል በክርስቶስ አማካይነት የተዘጋጀ መንገድ ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የድነትን ምንነት ማሳወቅ፤
2. ለሰው ልጆች ድነት ሲል ጌታ ኢየሱስ የከፈለውን ዋጋ ማሳየት፤
3. ከኢየሱስ ቤዛነት የተነሳ የሚገኘውን ድነት አጉልቶ በማሳየት፣ ያመነ ሁሉ ድነት እንደሚያገኝ ማረጋገጥ፤

### ትምህርቱ

1. ሰው ሁሉ ድነት ያስፈልገዋል፤
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23)
2. ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ ድነት ያስፈልገዋል፤
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:8)
3. ድነት ለማግኘት ሰው፥
   i. ኃጢአቱን ማወቅ፣ ራሱን ማዳን እንደማይቻለው ተረድቶ ንስሐ መግባት፣
      (የሐዋርያት ሥራ 16:30-31)

ii. ጌታ ኢየሱስ ለድነቱ የከፈለውን ዋጋ መገንዘብና በእምነት መቀበል፣
(የሐዋርያት ሥራ 16:32-34)

4. ንስሐ መግባት ማለት፥ ኃጢአትን ተገንዝቦ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን መጠየቅና ከኃጢአት መመለስ ማለት ነው፤
(1ኛ የዮሐንስ መልእክት 1:8-9)

5. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለድነታችን ያደረገው፥
   i. ለኃጢአት ስርየት ደሙን አፍስሷል፤
   (ወደ ዕብራውያን 9:11-14)
   ii. በኃጢአተኛው ሰው ምትክ ሞቷል፤
   (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5:2)

6. የድነት መንገዶች የሚመስሉ ግን ያልሆኑ በከፊል የሚከተሉት ናቸው፥
   i. መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅ ብቻውን፣ ጥቅሶችን በቃል ማስታወስ . . .
   ኒቆዲሞስ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያውቅ የሕግ መምህር ቢሆንም፣ ለመዳን ዳግም መወለድ እንደሚያስፈልገው ተነግሮታል፣
   (የዮሐንስ ወንጌል 3:3-10)
   ii. መልካም ሥራን በመሥራት ለመጽደቅ መሞከር፣
   (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-10፣ ትንቢተ ኢሳይያስ 64:6)
   ቆርኔሌዎስ ለድኾች የሚሰጥ ሰው ቢሆንም፣ ያዳነው ግን ይህ መልካም ድርጊቱ አልነበረም፣
   (የሐዋርያት ሥራ 10:4፤ 44-48)
   iii. መልካም ሰው ለመሆን መሞከር፣
   ቆርኔሌዎስ መልካም ሰው ቢሆንም፣ ጴጥሮስ ሄዶ ወንጌልን ሳይነግረውና ሳይቀበል በፊት የዳነ አልነበረም፣
   (የሐዋርያት ሥራ 10:1-4፤ 44-48)
   iv. የኦሪትን ሕግጋት በመጠበቅ ብቻ ለመጽደቅ መሞከር፣
   (ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16፣ 3:2-5)
   v. በጻድቃን፤ በሰማዕታትና በመላእክት አማላጅነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት መሞከር፣
   (የዮሐንስ ወንጌል 14:6፣ የሐዋርያት ሥራ 4:12፣ የሉቃስ ወንጌል 16:22-23፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 8:33-34፣ 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:3-5)
   vi. ከክርስቲያን ቤተ ሰብ መወለድ፣
   (የዮሐንስ ወንጌል 1:13)
   vii. የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችን መካፈል፤
   ይህንን ማድረግ መልካም ቢሆንም፣ አንድ ሰው ጌታ ኢየሱስን እስካልተቀበለ ድረስ መዳን አይችልም፤
   viii. ሃይማኖተኛ የሚያስመስሉ ልብሶችን መልበስና ጻድቅ መስሎ ለመታየት መሞከር፣
   ፈሪሳውያን ሥራዓት ጠባቂዎችና ሃይማኖተኛ መስለው የሚታዩ ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ግን በሥራቸው ድስ አልተሰኘም
   (የሉቃስ ወንጌል 11:39-41)

7. ከድነት በረከቶች መካከል በከፊል የሚከተሉት ናቸው፥
   i. በሰማይ መዝገብ ላይ የስማችን መጻፍ፣
   (ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 4:3፣ የዮሐንስ ራእይ 13:8)
   ii. አዲስ ፍጥረት መሆን፣
   (2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:17፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 3:10)
   iii. የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣
   (የዮሐንስ ወንጌል 1:12፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 4:6-7፣ 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 3:1)

iv. ከእውነተኛው አምላክ ጋር ኅብረትን ማድረግ መቻል፣
(1ኛ የዮሐንስ መልእክት 2:3፣ የዮሐንስ ወንጌል 14:21)

v. በእግዚአብሔር መንፈስ መታተም፣
(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:13፣ 4:30)

vi. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆን፣
(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6:19-20)

vii. የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መሆን፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 12:4-5፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:19)

viii. ከኃጢአት እና ከጨለማ ኃይል መዳን፣
(የሉቃስ ወንጌል 10:19፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-7፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:13-14)

ix. የዘላለም ሕይወት ማግኘት፣
(የዮሐንስ ወንጌል 3:16)

8. ሰው ድነት ማግኘቱን የሚያውቀው፥

i. በእግዚአብሔር ቃል፣
(1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:23)

ii. በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 8:16)

iii. በሕይወት በሚታይ ለውጥ፣

## (ወደ ገላትያ ሰዎች 5:22)

## ማጠቃለያ

ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ወደ ምድር የመጣው ለሰው ልጆች ድነት እንደሆነ የሚያምንና ኃጢአተኝነቱን አውቆ ንስሐ የሚገባ ሁሉ ከድነት በረከቶች ይቋደሳል። እናም የሚጠበቅብንን በማድረጋችን ማለትም በጌታ በማመናችን እነዚህን በረከቶች አግኝተናል። ስለሆነም፣ ስለመዳናችን ርግጠኞች ልንሆንና እንደሚገባ ልንመላለስ ያስፈልጋል።

## ጥያቄዎች

1. ድነት ምንድን ነው?
2. ድነት የሚያስፈልገው ማን ነው?
3. ድነት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?
4. ድነት ለማግኘት ሰው ማድረግ ያለበት ምንድን ነው?
5. ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?
6. ጌታ ኢየሱስ ለድነታችን ያደረገው ምንድን ነው?
7. ሰው ድነት ማግኘቱን በምን ያረጋግጣል?

## የጥናት ጥቅስ

**“በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።”** *የሐዋርያት ሥራ 16:31*

**“ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤”** *ወደ ሮሜ ሰዎች 10:9*

# ትምህርት አምስት

## የሰው ማንነት በክርስቶስ

### የንባብ ክፍል

*የዮሐንስ ወንጌል 8:32*

**"እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።"**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

የዮሐንስ ወንጌል 17:22-23፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 3:16-19፣ የዮሐንስ ራእይ 5:9-10፣ ወደ ዕብራውያን 10:17፣ 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:20

### መግቢያ

ካደረግነው አንዳች ነገር የተነሳ ሳይሆን፤ ራሱ እግዚአብሔር ካለው ፍቅር የተነሳ ገና በኀጢአታችን እና በበዳላችን ሙታን ሆነን ሳለን እግዚአብሔር ወደደን። ከወደደንም ከዚህ ፍቅር የተነሳ በክርስቶስ በማመናችን አዲስ ፍጥረት አደረገን። ህያዋን እና ለእርሱ የተለየን ሆንን። ይህም በውስጣችን አዲስ በክርስቶስ የሆነን ማንነት ፈጠረ።

### የቃሉ ትርጉም

"የሰው ማንነት በክርስቶስ" - ይህ ማለት የሰው ልጅ በክርስቶስ ከማመኑ የተነሳ የሆነውን እና የገኘውን አዲስ ማንነት ማለት ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. በክርስቶስ ያገኘነውን አዲስ ማንነት ማሳወቅ፤
2. በክርስቶስ ያገኘነውን ጥቅሞች ማስገንዘብ፤
3. በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆናችንን ማሳየት፤

### ትምህርቱ

1. በእግዚአብሔር የዘላለም ፍቅር ተወደናል፤
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:8፣ የዮሐንስ ወንጌል 17:22-23፣ 15:13፤ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 3:16-19)
2. በክርስቶስ የከበረ ደም በዋጋ ተገዝተናል፤
   (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6:19-20፣ የዮሐንስ ራእይ 5:9-10፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 5:8)
3. በክርስቶስ ጸድቀን ከኩነኔ ሁሉ ነጻ ወጥተናል፤
   (ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 3:22,25፤ 5:17)
4. በክርስቶስ ለዘላለም የኀጢአትን ይቅርታ አግኝተናል፤
   (የዮሐንስ ወንጌል 1:29፣ የማቴዎስ ወንጌል 26:28፣ ወደ ዕብራውያን 10:17)
5. በክርስቶስ ስራ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን አግኝተናል፤
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 5:1)

6. የእግዚአብሔር ልጆች ሆንን፣ ዳግም ተወለድን፣ አዲስ ፍጥረት ሆንን፤
   (2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:17፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:24፣ የዮሐንስ ወንጌል 1:12-13፣ 3:5-7፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:20
7. የእግዚአብሔር አገልጋይ ካህናት ሆንን፤
   (1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:5,9፣ የዮሐንስ ራእይ 1:5-6)
8. የእግዚአብሔር ወዳጆች ሆንን፣
   (የዮሐንስ ወንጌል 15:15)
9. የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሆንን፤
   (2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:20)

## ማጠቃለያ

በክርስቶስ በሆነ ስራ እግዚአብሄር እኛን የእርሱ ልጆች አደረገን። ከዚህም የተነሳ በክርስቶስ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባረከን። "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:3

## ጥያቄዎች

1. በክርስቶስ ያገኘነው አዲስ ማንነት ምንድን ነው?
2. በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
3. በክርስቶስ ያገኘናቸው ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

## የጥናት ጥቅስ

**"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።"** *የዮሐንስ ራእይ 1:5-6*

# ትምህርት ስድስት

## እምነት

### የንባብ ክፍል

*ወደ ሮሜ ሰዎች 4:20-21*

**“ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፥ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፥ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም።”**

*ወደ ሮሜ ሰዎች 4:4-5*

**“ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ወደ ሮሜ ሰዎች 1:16-32፣ 4:16-22፣ 5:1-11፣ 10:14-17፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 3:1-14፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:8-9፣ የያዕቆብ መልእክት 2:14-26፣ ወደ ዕብራውያን 11

### መግቢያ

እምነት በአምላክ ፍጹም ተስፋ ማድረግ ሲሆን፤ ይህም እምነት ስራን ያስከትላል። መጽሐፍ ቅዱስ “እምነት” ሲል ስለዚህ እውነተኛ እምነት ነው። ሰው በእምነት ሲኖር በእግዚአብሔር ቃል ይመራል። ምንም እንኳን ነገሩ የማይቻል ወይንም የማይሆን ቢመስልም አማኙ ይታዘዛል፤ ሳይጠራጠርም ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር ቃሉን እስኪፈጽም ድረስ በተስፋ ይኖራል።

### የቃሉ ትርጉም

“እምነት” ማለት “ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።”ወደ ዕብራውያን 11:1 እምነት የእግዚአንሔር ስጦታ ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የእምነትን ምንነት ማሳየት፤
2. የእምነትን አስፈላጊነት ማስገንዘብ፤
3. የእምነትን ምንጭ ማሳወቅ፤

### ትምህርቱ

1. የእምነት ዋነኛ አስፈላጊነት፥ እግዚአብሔርን “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤” ወደ ዕብራውያን 11:6
    i. መዳን በእምነት ነው፣
       (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:8፣ የማርቆስ ወንጌል 16:16፣ የሐዋርያት ሥራ 16:31፣ የዮሐንስ ወንጌል 1:12፣ 5:24፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 4:5፣ 5:1፣ ወደ ዕብራውያን 10:39)

ii. የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ በእምነት ተቀበልን፣
(ወደ ገላትያ ሰዎች 3:14፣ የዮሐንስ ወንጌል 7:39)
iii. በእምነት ተቀደስን፣
(የሐዋርያት ሥራ 15:9፣ 26:18)
iv. በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠበቅን፣
(1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:3-5፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 11:20፣ 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:24)
v. በእምነት ነፍስ ፈጽሞ በሰላም ተጠበቀች፣
(ትንቢተ ኢሳይያስ 26:3፣ ወደ ዕብራውያን 4:3)
vi. በእምነት ተፈወስን፣
(የያዕቆብ መልእክት 5:14፣ የሐዋርያት ሥራ 14:9)
vii. ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው፣
(1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5:4)
viii. የክርስትና ኑሮአችንን የምንኖረው በእምነት ነው፣
(ትንቢተ ዕንባቆም 2:4፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 1:17፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 3:11፣ 2:20፣ ወደ ዕብራውያን 10:38)

2. የእምነት ምንነት፥ “እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።”
(ወደ ዕብራውያን 11:1)
3. የእምነት ምንጭ፥ የእግዚአብሔር ቃል ነው።
(ወደ ሮሜ ሰዎች 10:17)

## ማጠቃለያ

እምነት ለአማኝ ዋነኛና እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልምና። መዳን በእምነት ብቻ ነው፣ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ በእምነት ተቀበልን፣ በእምነት ተቀደስን፣ በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ተጠበቅን፣ በእምነት ነፍሳችን ፈጽሞ በሰላም ተጠበቀች፣ በእምነት ተፈወስን፣ ዓለምንም በእምነታችን አሸነፍን፤ ይህንንም እምነት ከእግዚአብሔር ተቀበልን።

## ጥያቄዎች

1. እምነት ምን ማለት ነው?
2. እምነትን ከምን አገኘን?
3. በማመናችን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምን ሆነልን?

## የጥናት ጥቅስ

**“እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።”** *ወደ ሮሜ ሰዎች 10:17*

# ትምህርት ሰባት

## መጽደቅ

### የንባብ ክፍል

*ወደ ሮሜ ሰዎች 3:21*

**“አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥”**

*ወደ ሮሜ ሰዎች 4:4-5*

**“ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ወደ ሮሜ ሰዎች 3:21-28፣ 5:12-19፣ 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:16-21፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:11-21፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-10፣ ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 3:7-11

### መግቢያ

ኃጢአተኛ ሕጉን ሳይፈጽም ሲቀር በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ ሊቆም እንዴት ይችላል? ጽድቅ፥ ማለት ሕግን መፈጸም እንደ ሕግ መኖርና መመራት፣ ትክክለኛነት፣ እውነት ማለት ነው። መጽደቅ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር ኃጢያታችን የተሰረየ መሆኑን እና የክርስቶስ ጽድቅ የእኛ ጽድቅ መሆኑን የሚቆጥርበት እና በእርሱ ፊት ጻድቃን እንደሆንን የሚያውጅበት ቅጽበታዊ የሆነ ሕጋዊ ተግባር ነው። ትክክለኛ የሆነ የመጽደቅ ግንዛቤ ለክርስትና እምነት በጣም ወሳኝ ነው። መቤዤትን ለእኛ እውን በማድረግ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ለእምነታችን ምላሽ፤ ተስፋ በገባው መሰረት ኀጢአታችን ይቅር የተባለ መሆኑን በማወጅ አጸደቀን። ከሕግ ጋር ያለንን ግንኙነት በማስመልከት ፈጽሞ ይቅር መባላችንን፤ ከእንግዲህ ቅጣት የማይደርስብን መሆኑን አወጀ። ጻድቅ ሆነን ተቆጠርን።

### የቃሉ ትርጉም

መጽደቅ፥ ማለት እግዚአብሔር ኃጢያታችን የተሰረየ መሆኑን እና የክርስቶስ ጽድቅ የእኛ ጽድቅ መሆኑን የሚቆጥርበት እና በእርሱ ፊት ጻድቃን እንደሆንን የሚያውጅበት ቅጽበታዊ የሆነ ሕጋዊ ተግባር ነው። መጽደቅ እኛን በተመለከተ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የጽድቅን ምንነት ማስረዳት፤
2. እንዴት ኃጢአተኛው ሕጉን ሳይፈጽም ሲቀር በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅ ሊቆም እንደቻለ ማስረዳት፤
3. ሰው በእምነት መጽደቁን ማሳየት፤

### ትምህርቱ

1. የሕግን ሥራ በመሥራት ማንም አይጸድቅም፣
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:20፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16)

2. እግዚአብሔር እንዲሁ በፍቅሩ ኃጢአተኞችን ለማዳን ስለወሰነ፣ ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ ይጸድቃል፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3:24፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:8)
3. ሰው በክርስቶስ ደም ይጸድቃል፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3:25፤ 5:9፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 3:13)
4. ሰው በእምነት ይጸድቃል፣
   i. በእግዚአብሔር ሲያምን ተስፋውን ሁሉ በጌታ ላይ ይጥላል፣
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 3:25፣ 5:1፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16)
   ii. ሲያምን እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል፣
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 4:3-5,22-25፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 3:6-8)
   iii. የጽድቅ መቆጠር እና የኃጢአት አለመቆጠር የተያያዙ ናቸው፣
   (ወደ ሮሜ ሰዎች 4:6-8)
   iv. ለአማኝ የሚቆጠርለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፣ በክርስቶስ ጽድቅ ይገኛል፣
   (ትንቢተ ኤርምያስ 23:6፣ ወደ ሮሜ ሰዎች 3:21፣ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:30-31፣ 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:21፣ 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:1)
5. ስው ያለ ሕግ ሥራ ይጸድቃል፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3:28፣ 4:5)
6. መጽደቅ የሚታወጀው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3:20,26-28፣ 5:1፣ 8:30፣ 10:4,10፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16፣ 3:24)
7. የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሊቀለብስ የሚችል አንድም ኃይል የለም፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 8:33-34)
8. እግዚአብሔር የክርስቶስ ጽድቅ ለእኛ እንዲቆጠር አደረገ፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 4፡3,5-6፣ 5:17)
9. መጽደቅ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ነው፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 3:23-24)
10. እግዚአብሔር ያጸደቀን በክርስቶስ ላይ ባለን እምነት ነው፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 5:1፣ ወደ ገላትያ ሰዎች 2:16)
11. የጸደቅነው በክርስቶስ መልካም ሥራ ብቻ ነው፣
(ወደ ሮሜ ሰዎች 5:17-19)

## ማጠቃለያ

መጽደቅ በእምነት ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ከቶ ማጽደቅ አንችልም። ድነት በእምነት ብቻ የሚቀበሉት ነጻ የጸጋ ስጦታ ነው፤ እግዚአብሔርም በክርስቶስ መልካም ስራ የተሰረየውን ኀጢአት ቅጣት እንደማያስከፍለን በማረጋገጥ የክርስቶስን ጽድቅ ለእኛ በማድረግ መጽደቃችንን አወጀ።

## ጥያቄዎች

1. ጽድቅ ማለት ምን ማለት ነው?
2. መጽደቅ ማለት ምን ማለት ነው?
3. የተቆጠረልን ጽድቅ የማን ጽድቅ ነው?
4. ለመጽደቃችን ያደረገነው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

## የጥናት ጥቅስ

**"ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ። ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና።"** *ወደ ሮሜ ሰዎች 3:27-28*

# ትምህርት ስምንት

## ቅድስና

### የንባብ ክፍል

*1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:15-16*

**“ዳሩ ግን፦ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

ዕብራውያን 12:14፣ ኦሪት ዘሌዋውያን 19:2፣ ወደ ቆላስይስ ሰዎች 3:12-15

### መግቢያ

አዲስ የተወለደ ሕጻን በተወለደ ጊዜ ሰውነቱ ይታጠባል፤ ይጸዳልም። ነገር ግን፣ ጽዳቱ በዚህ ብቻ አያበቃም፣ ሁልጊዜ ንጹሕ ይሆን ዘንድ በየጊዜው መታጠብ ያስፈልገዋል። ዳግም የተወለደ አማኝም እንዲሁ ነው፤ ጌታን በተቀበለበትና ንስሐ በገባበት ጊዜ ኃጢአቱ ሁሉ በክርስቶስ ደም ይታጠባል። ነገር ግን፣ ዘወትር ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሁልጊዜ መቀደስ ይኖርበታል።

በተመሳሳይ ሁኔታም ቅድስና በአማኝ ሕይወት ውስጥ የማያቋርጥ ሂደት ነው። ጌታን አምኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በክርስቶስ ደም ከነጻበት ጊዜ ጀምሮ እየተቀደሰ፣ በባሕርዩም ጌታውን እየመሰለ ሊያድግ ይገባል። ጌታ ሲመጣ ወይም በዚህ ዓለም የመኖሪያ ዘመኑ ሲያበቃ ደግሞ ፍጹም ቅዱስ ይሆናል። በዚህ ክፍልም የመቀደስን ምንነት፣ የቅድስና ደረጃዎችን፣ ለመቀደስ የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንዲሁም መቀደስ የሚያስከትላቸውን በረከቶችንና አለመቀደስ የሚያመጣውን ቅጣት አጠር አድርገን ለመመልከት እንሞክራለን።

### የቃሉ ትርጉም

ቅድስና፥ ለእግዚአብሔር መለየት ማለት ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የቅድስናን ምንነት ማሳወቅ፣
2. የመቀደስን ምክንያትና አስፈላጊነት እንደዚሁም ለመቀደስ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማስገንዘብ፣
3. ከመቀደስ የሚገኘን በረከት እንዲሁም ያለመቀደስን ጉዳት በማሳየት በፈቃድ ራስን ለጌታ መቀደስን ማበረታታት ነው፣

### ትምህርቱ

1. መቀደስ ማለት፣
   i. ለእግዚአብሔር አገልግሎት መለየት፣
      ኦሪት ዘሌዋውያን 19:2
   ii. እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት መኖር፣
      ወደ ቆላስይስ ሰዎች 3:12-15

iii. ክፉና ርኩስ ከሆነ ነገር መራቅ፣
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 3:2፣ 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:21

2. የቅድስና ደረጃዎች፣ ሦስት ሲሆኑ እነርሱም፥
   i. ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነበት ቅጽበት ይቀደሳል፣
   1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6:9-11፣ ወደ ዕብራውያን 10:19፣ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:2
   ii. አማኝ በየዕለቱ በቅድስና እያደገ ይሄዳል፣
   1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:18፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:15
   iii. ጌታ በክብር ሲመጣ የአማኞች ቅድስና ፍጹም ይሆናል
   ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 3:21
3. በቅድስና ለመኖር የሚረዱ ነገሮች፣
   i. መጸለይ፣
   ወደ ሮሜ ሰዎች 12:12
   ii. የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፣
   መዝሙረ ዳዊት 119:9-16
   iii. እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር፣
   የዮሐንስ ወንጌል 8:31
   iv. ከአማኞች ጋር ኅብረት ማድረግ፣
4. መቀደስ ለምን፣
   i. እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ስለሆነ፣
   1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:15-16
   ii. እግዚአብሔር ቅዱስ እንድንሆን ስለሚፈልግ፣
   1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 4:3
   iii. ከእግዚአብሄር ጋር የማያቋርጥ ኅብራት ላማድረግ እና በፈቃዱ ለመኖር፣
   ወደ ዕብራውያን 12:14
   iv. ከአማኞች ጋር ኅብረትን ለማድረግ፣
5. በመቀደስ የሚገኙ በረከቶች
   i. የእግዚአብሔርን ማንነት ማወቅ ያስችላል፣
   ወደ ዕብራውያን 12:14
   ii. እግዚአብሄርን ለማገልገል የሚያስችል ብቃት ይጨምራል፣
   2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:21
   iii. ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ ያስችላል፣
   1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:11-12
6. ያለመቀደስ ችግር፣
   i. መንፈሳዊ ሕይወትን ያደክማል፣
   ii. ቅጣትን ያስከትላል፣
   መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 29:1-11፣ ወደ ዕብራውያን 12:10-11

## ማጠቃለያ

መቀደስ ሕይወትን ለእግዚአብሔር መለየት ነው። ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ርዳታና በራሳችን ፈቃድ የምናደርገው ነው። እግዚአብሔር ቀድሶናል ደግሞም ይቀድሰናል፣ እኛም ደግሞ ቅድስናችንን ለመፈጸም መትጋት ይኖርብናል። ስለዚህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖርና ለሌሎች በረከት ለመሆን በፈቃዳችን ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንቀድስ።

## ጥያቄዎች

1. ቅድስና ማለት ምን ማለት ነው?
2. አንድ ሰው የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር ምን ማድረግ አለበት?
3. የመቀደስ ውጤት ምንድን ነው?
4. አለመቀደስ ምንን ያስከትላል?

## የጥናት ጥቅስ

**“ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።”**
*ዕብራውያን 12:14*

# ትምህርት ዘጠኝ

## ጸሎት

### የንባብ ክፍል

*1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:17-18*

**“ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

*መዝሙረ ዳዊት 51፣ የያዕቆብ መልእክት 5:16፣ 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:1-2*

### መግቢያ

አማኞች በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ከተሰጣቸው ልዩ የልጅነት መብቶች መካከል አንዱ፤ በጸሎት ከእግዚአብሔር ከአባታቸው ጋር መገናኘት ነው። ከልብ በማመን የሚጸለይን ጸሎት ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያደምጥና እንደ ፈቃዱም ምላሽን እንደሚሰጥ በቃሉ ተስፋን ሰጥቶአል። በዚህ ጥናት የጸሎት ዓይነቶችን፣ ወደ ማን እንደሚጸለይ፣ አንዳንድ ጸሎቶች ለምን ምላሽ እንደማያገኙ፣ የመጸለይን ጥቅምና ያለመጸለይን ጉዳት እንዲሁም ጸሎትን በተመለከተ ሌሎች ጠቃሚ ነጥቦችን አጠር ባለ መልኩ ለማየት እንሞክራለን።

### የቃሉ ትርጉም

ጸሎት፥ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሚደረግ ኅብረት ወይም ንግግር ነው።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የጸሎት ምንነትን ማሳወቅ፣
2. በጸሎት አማካኝነት የሚመጡ በረከቶችን በማሳየት ተግቶ መጸለይን ማበረታታት፣

### ትምህርቱ

1. የጸሎት ዓይነቶች፣
   i. የንስሐ ጸሎት፥ በደለኝነትን ወንም ኃጢአተኝነትን በመገንዘብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ለመቀበል የሚደረግ ጸሎት ነው።
   *መዝሙረ ዳዊት 51:1-11*
   ii. የልመና ጸሎት፥ ከእግዚአብሔር አንድን ነገር ለማግኘት በፊቱ የሚቀርብ ጥያቄ ነው።
   *የማቴዎስ ወንጌል 7:7*
   iii. የውዳሴ ጸሎት፥ የእግዚአብሔር አምላክነት፣ ጌትነት ደግሞም ያደረገውን ነገር በማሰብ፣ ለእርሱ ክብር፣ በስግደትና በአድናቆት የሚቀርብበት ጸሎት ነው።
   *መዝሙረ ዳዊት 135:1-21*
   iv. የምስጋና ጸሎት፥ እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር በማሰብና በመዘርዘር እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ጸሎት ነው።

v. የምልጃ ጸሎት፥ በምድር ላይ፣ በአገራት መካከል፣ በሰዎች ሕይወት ውስጥ . . . ወዘተ ያሉ ችግሮችን በማሰብ እግዚአብሔር መፍትሔን እንዲሰጥ እንዲባርክና እንዲያጽናና . . . ወዘተ የሚጸለይ ጸሎት ነው።
የያዕቆብ መልእክት 5:16፣ 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:1-2

2. ወደማን እንጸልይ፥ ወደ እግዚአብሔር ወደ አባታችን፣
የማቴዎስ ወንጌል 6:5፣ ወደ ኤፌሶን ሰዎች 3:14-15

3. የጸሎት ጥቅም፣ ጸሎት . . .
   i. እግዚአብሔርን ማነጋገሪያ መንገድ ነው፣
   የሉቃስ ወንጌል 22:41-43
   ii. ሰይጣንን ድል መንሻ ነው፣
   ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:11-18፣ የያዕቆብ መልእክት 4:7-8
   iii. በረከት መቀበያ ነው፣
   መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 1:19-20
   iv. እግዚአብሔርን ማክበሪያ ነው፣
   መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 7:18-29

4. ጸሎት መልስን የማያገኘው፣
   i. ኃጢአትን በመሥራት፣
   መዝሙረ ዳዊት 66:18፣ ትንቢተ ኢሳይያስ 59:1-2
   ii. ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዝ፣
   መጽሐፈ ምሳሌ 25:9
   iii. ይቅርታ ባለማድረግ፣
   የማቴዎስ ወንጌል 5:22-24፣ 6:12-15
   iv. በእምነት ማነስ፣
   ወደ ዕብራውያን 11:6፣ የያዕቆብ መልእክት 1:6
   v. በክፉ ምኞት ወይንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባልሆነ ጉዳይ ላይ በመጸለይ፣
   የያዕቆብ መልእክት 4:3

5. ጸሎትን በተመለከተ ማወቅ የሚገባን፣
   i. ጊዜ አይወስነውም፣
   የሉቃስ ወንጌል 18:1፣ 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:17
   ii. ቦታ አይወስነውም፣
   የዮሐንስ ወንጌል 4:24-31
   iii. በእምነት ሊደራግ ይገባል፣
   ወደ ዕብራውያን 11:6
   iv. በኢየሱስ ስም ሥልጣን ሊጸለይ ይገባል፣
   የዮሐንስ ወንጌል 14:13
   v. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊጸለይ ይገባል፣
   1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5:14-15
   vi. ያለመታከት ሊጸለይ ይገባል፣
   መዝሙረ ዳዊት 40:1፣ የሉቃስ ወንጌል 18:1-18፣ የያዕቆብ መልእክት 5:16

6. ያለመጸለይ ጉዳት፣
   i. ለጠላት ጥቃት ያጋልጣል፣
   1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5:8
   ii. ለፈተና ያጋልጣል፣
   የማቴዎስ ወንጌል 26:41

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔርን በጸሎት አማካይነት ማነጋገር ለእኛ ለልጆቹ የተሰጠን ልዩ መብት ነው። እኛም ደግሞ ጸሎታችን መልስ እንዲያገኙ የሚያደርጉ ነገሮችን በማስወገድ በመብታችን ተጠቃሚ ልንሆንና ሰማያዊ አባታችንን በየዕለቱ ልናነጋግረው ይገባናል።

## ጥያቄዎች

1. ጸሎት ምንድን ነው?
2. በመጸላያችን የምናገኛቸው በረከቶች ምንድን ናቸው?
3. ጸሎት የእግዚአብሔር ልጆች መብት ነው፤ የዚህ መብት ተጠቃሚዎች ነኝ?
4. ጸሎት ቦታ አይወስነውም ሲባል ምን ማለት ነው?
5. በትምህርቱ መሰረት የጸሎት ዓይነቶችን ዘርዝሩ፥

## የጥናት ጥቅስ

**"ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።"** *ወደ ፊልጶስዩስ ሰዎች 4:6*

# ትምህርት  አስር

## መከራ

### የንባብ ክፍል

*የማቴዎስ ወንጌል 16:24*

**“በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።”**

### ረዳት ጥቅሶች

**ለተጨማሪ ጥናትና ለማሰላሰል የሚከተለውን ይመልከቱ፥**

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:12፣ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:21-24

### መግቢያ

የማቴዎስ ወንጌል 7:13-14 “በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።” በዚህ ክፍል ላይ ሁለት ዓይነት የሕይወት መንገዶች እንዳሉ ጌታችን ተናግሯል። አንደኛው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነው። በሰፊው መንገድ ብዙዎች ይጓዙበታል፤ ምክንያቱም ለማለፍ ቀላልና መከራ የማይበዛበት ስለሆነ ነው። መጨረሻው ግን ጥፋትና የዘላለም ሞት ነው። ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ላይ የተጠቀሰውና በሰፊ መንገድ የተመሰለው፣ ክርስቶስን ያላመኑ ሰዎች የሚኖሩት የዓለማዊነት ሕይወት ነው።

ሁለተኛው መንገድ ከመጀመሪያው ፈጽሞ የተለየ ነው። ጠባብና የማይመች፣ ብዙ ፈተናም ያለበት ነው። ከዚህም የተነሣ ብዙ ሰዎች ይጓዙበት ዘንድ አይመርጡትም፤ በርትተው የሚሄዱበት ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይደርሳሉ። ይህም ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች መርጠው የሚጓዙበት የክርስትና ሕይወት ተምሳሌት ነው።

በዚህ ጥናት የምናየው በዚህ በጠባብ መንገድ የሚጓዙ አማኞች ስለሚያጋጥማቸው ፈተና ነው። ቅዱሳን ለምን መከራን እንደሚቀበሉ፣ በመከራ ወቅት ምን ማድረግ እንደሚገባ፣ በመከራ ላይ ድልን እንዴት መቀዳጀት እንደሚቻልና መከራ ስለሚያስከትላቸው በረከቶች በአጭሩ እንመለከታለን።

### የቃሉ ትርጉም

መከራ ወይንም ስደት፥ አንድ አማኝ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመኑ ምክንያት የሚደርስበት ሲሆን፤ ይህም በክርስትና መንገድ ላይ ክርስቶስን እየተከተለ የሚሄድ መሆኑን ያመለክታል።

### የትምህርቱ ዋና ዓላማ

1. የክርስትና መንገድ ፈተና ያለበት መሆኑን ማሳወቅ፣
2. አማኞች ከእምነታቸው የተነሣ የሚገጥማቸውን ፈተና እንዴት መቋቋም እንዳለባቸው ማስረዳት፣
3. ከመከራ በኋላ የሚገኘውን በረከት በማሳየት በፈተና ወቅት መጽናትና መጽናናት እንደሚያስፈልግ ማስገንዘብ ነው፣

## ትምህርቱ

1. ቅዱሳን መከራን የሚቀበሉት፥
    i. ጌታ ራሱ መከራን ስለተቀበለ፣
    የማቴዎስ ወንጌል 26:47-68፣ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:21-24
    ii. የእምነት አባቶች ብዙ መከራ ስለተቀበሉ፣
    የሐዋርያት ሥራ 5:27-42፣ ወደ ዕብራውያን 11:32-38
    iii. መከራ እንደሚደርስብን ጌታ ስለተናገረ፣
    የማቴዎስ ወንጌል 24:9-14፣ የዮሐንስ ወንጌል 16:2
    iv. መከራ የክርስትና አንዱ ክፍል ስለሆነ፣
    2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:12
2. መከራ ሲደርስ ማድረግ ያለብን፥
    i. በእግዚአብሔር መታመን፣
    1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 4:19
    ii. ፍርዱን ለጌታ መስጠት፣
    ወደ ሮሜ ሰዎች 12:14-21
    iii. ብድራትን በማሰብ መጽናናት፣
    የያዕቆብ መልእክት 1:12፣ 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5:10
    iv. እግዚአብሔርን ማመስገን፣
    1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 4:16
    v. ያለማቋረጥ መጸለይ፣
    ወደ ሮሜ ሰዎች 12:12፣ የያዕቆብ መልእክት 5:13
    vi. በመከራ ውስጥ እግዚአብሔር ሊያስተምረን የፈለገውን ነገር ማስተዋል፣
3. መከራን ደግሞ ማለፍ የምንችለው፥
    i. በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ፣
    የዮሐንስ ወንጌል 14:15-16፣ የዮሐንስ ወንጌል 16:12-15
    ii. ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ በመረዳት፣
    የማቴዎስ ወንጌል 28:19-20፣ 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4:16-18
    iii. በእግዚአብሔር ጥበቃ፣
    ኦሪት ዘፍጥረት 28:15፣ የዮሐንስ ወንጌል 10:27-30
    iv. በመጸለይ፣
    የያዕቆብ መልእክት 5:13
4. ከመከራ የሚገኙ ፍሬዎች፥
    i. ትዕግሥትና ብስለትን ማግኘት፣
    2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1:4
    ii. ከእግዚአብሔር ብድራትን ማግኘት፣
    የማቴዎስ ወንጌል 5:10-12
    iii. የሕይወት አክሊል፣
    የያዕቆብ መልእክት 1:12፣ የዮሐንስ ራእይ 2:10
    iv. ብፁዕ ወይንም የተመሰገነ መሆን፣
    1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 4:14
5. መከራን አስመልክቶ ሊታወቁ የሚገባቸው ነገሮች፥
    i. ሰው በገዛ ጥፋቱ መከራን በራሱ ላይ ሊያመጣ ይችላል፣
    የያዕቆብ መልእክት 1:14
    ii. በኃጢአት ምክንያት መከራ ሊመጣ ይችላል፣
    መዝሙረ ዳዊት 10

## ማጠቃለያ

መከራ የክርስትና ሕይወት ውበት ነው። መከራ በሁሉም አማኞች ሕይወት ውስጥ ያልፋል። በመከራችን ወቅትም እግዚአብሔር አብሮን በመሆን ያግዘናል። የሚደርስብንን መከራ ታግሠን ማለፍ ከቻልን ብዙ በረከቶችን እናገኛለን። ስለዚህም መከራ ሲገጥመን ወደ ኋላ ማፈግፈግ ሳይሆን ጌታን ታምነን ወደፊት በእምነት ልንራመድ ይገባናል። የተጠራነው በክርስቶስ ኢየሱስ ልናምን ብቻ ሳይሆን፣ መከራም እንድንቀበል ነው።

## ጥያቄዎች

1. መከራ ወይንም ስደት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጌታን ከመከተላችን የተነሳ የሚደርስብን ችግር አለ? እንዴት እንወጣው?
3. መከራ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ምን ጥቅም አለው?
4. እንድ ክርስቲያን በመከራ ወይም በስደት ጊዜ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?

## የጥናት ጥቅስ

**“ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ።”** *1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 4:14*

# ዋቢ መጻሕፍት

*The Amharic Bible (1962) [የድሮው ትርጉም]. The Bible Society of Ethiopia. አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ*

*የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር (1987). የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት. አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ*

*Grudem, W. A. (2004). Systematic theology: an introduction to biblical doctrine. Leicester, England; Grand Rapids, MI: Inter-Varsity Press; Zondervan Pub. House.*

*Manunsell, Collin. The Doctrine of God (Amharic). Addis Ababa: Ethiopia Book Center, 2003*

*Manunsell, Collin. The Doctrine of Christ (Amharic). Addis Ababa: Ethiopia Book Center, 2003*

*Manunsell, Collin. The Doctrine of Holy Spirit (Amharic). Addis Ababa: Ethiopia Book Center, 2003*

*Berkhof, L. (1938). Systematic theology. Grand Rapids, MI: Wm. B. Eerdmans publishing co.*

*በጸጋ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን (2001). ድነት. አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ*

*Erickson, M. J. (2013). Christian Theology (3rd ed., p. 604). Grand Rapids, MI: Baker Academic.*

*Duffield, G. P., & Van Cleave, N. M.. Foundations of Pentecostal theology (p. 457). Los Angeles, CA: L.I.F.E. Bible College.*

*Sproul, R. C. (2014). Everyone's a Theologian: An Introduction to Systematic Theology. Orlando, FL: Reformation Trust.*

*Sproul, R. C. (1992). Essential truths of the Christian faith. Wheaton, IL: Tyndale House.*

*Ryrie, C. C. (1999). Basic Theology: A Popular Systematic Guide to Understanding Biblical Truth. Chicago, IL: Moody Press.*

*Packer, J. I. (1993). Concise theology: a guide to historic Christian beliefs. Wheaton, IL: Tyndale House.*